
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ታይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ሰንበት ትምህርት ቤት የተሰጠ

የነገረ ሃይማኖት ኮርስ



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ነሐሴ ፲ ፪፣ ፳ ፻ ፲ ፯ ዓ.ም

ነገረ ሃይማኖት

አለ ሃይማኖት የሚናገር የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ነው። ሃይማኖት ሃይመነ፡ አመነ፡ አሳመነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ምዕላድ ሲሆን ትርጉሙ ማመን፡ መታመን ማለት ነው። ማመን ማለትም የዘለዓለም ፈጣሪ፡ አስተዳዳሪ፡ ለመጋቢ አላት ብሎ ሳይጠራጠሩ ባለማና አለመቅለል ነው። መታመን ማለት ደግሞ ያመንነውን ነገር ለእንደለት መመሰክርና በተግባር ማዋል ነው። የትምህርተ ሃይማኖት መሠረቱ የፈጣሪ መኖር ነው።

ሃይማኖትና ፍልስፍና

ፍልስፍና "ፈለሰፈ፡ጥበብ ተናገረ" ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ጥበብ ማለት ነው። ጥበብን መውደድም ፍልስፍና ይባላል። ፍልስፍና ሁለት ዐበይት ክፍሎች አሉት። እነዚህም ሐሳባዊ ፍልስፍና እና ተግባራዊ ፍልስፍና ናቸው። ለሐሳባዊ ፍልስፍና ውስጥ የሚጠኑት ግኖሶሎጂ (Gnosiology) እና ሜታፊዚክስ (Methaphysics) ናቸው። ለተግባራዊ ፍልስፍና ውስጥ የሚጠኑት ደግሞ ሠነ አመክንዮ (Logic)፡ ሥነ ምግባር (Moral philosophy/Ethics)፡ እና ለሠነ ውለት (Aesthetics) ናቸው።

ለግኖሶሎጂ የሚጠኑ ጉዳዮች

- የዕውቀታችን ወሰንና ኃይል እስከምን ድረስ ነው የሚለው
- የዕውቀታችን ምና ምንጫ ምንድን ነው የሚለው
- ዕውቀታችን የሚያርፍበትና ሀሳባችን ሁሉ የሚወድቅባት የውጫ ነገር ምን እንደሆነ

የዕውቀታችን ወሰንና ኃይል እስከምን ድረስ ነው ለሚለው ሥር አምስት ጉዳዮች አሉ።

1. ዶግማቲዝም
2. ስኬፕቲሲዝም
3. ኘራግማቲዝም
4. ፓዘቲቪዝም
5. ክሪትሲዝም

የዕውቀት ምንጫ ምንድን ነው ለሚለው ሦስት እይታዎች አሉ።

1. ኢምፕሪሲዝም
2. ራሽናሊዝም
3. ክሪቲሲዝም

በሜታፊዚክስ የሚጠኑ ጉዳዮች

በሜታፊዚክስ ላይ ጥናት ሁለት ጉዳዮች ይጠናሉ እነዚህም አንቶሎጂና ኮዝሞሎጂ ናቸው። አንቶሎጂ በዚህ ዓለም ያሉ ነገሮች ከምን ተሠሩ መሰኻኮው ምንድን ነው የሚለውን ያብራራል።

ስለእንዴለመጀ ሙሉና አራት አሳቤዎች ይጠናሉ።

1- ማቴሪያሊዝም:- ለዓለም ያለ ነገር ሁሉ ቁሳዊ ነው።
2- አይዲያሊዝም:- ለዓለም ያለ ነገር ሁሉ መንፈሳ ነው።
3. ፓራሌሊዝም:- ለዓለም ሙሉና ቁሳም መንፈሳም አለ
4. ዱያሊዝም:- የመንፈሳ ፈጣሪ ሌላ የቁሳ ፈጣሪ ሌላ ነው ይላል።

ስንዝም ስለመጀ ዓለም ስለሚካሄድበት ሥሉ ለሠርዓትና ስለ ሕይወት አገናኝት ይገለጻል። ዓለም ስለሚካሄድበት ሥሉ ለሠርዓት የሚከተሉት አሳቤዎች ይጠናሉ።

1. ሜካኒዝም:- የፈጣሪን ህልውና የሚክድ አሳሌ ነው
2. ቲሎሎጂዝም:- ይህም የፈጣሪን ህልውና አይቀበልም
3. ሃዝምኅኒ:- ዓለም የተፈጠረው ለእግዚአብሔር እንደሆነ ይገለጻል።

የሕይወት አገኛኘት

ለሕይወት አገናኝት ዙሪያ ሁለት አሳቤዎች አሉ። እነዚህም:-

1. ዝግመተ ለውጥ (Evolution)
2. ቲዮሎጂ

ለዝግመተ ለውጥ አሳሌ የሚመሩት ዓለም አሁን ያለችበትን ቅርጽ ለትይዝ የቻለችው ለአካባቢ ተጽእኖ (Natural Selection) ፣ ለውርስ (Heredity) ና ለሌሎች ተጽእኖዎች ነው ይላሉ። ስለ እግዚአብሔር መኖርና ስዓለሙ ጋር ስላለው ግንኙነት አምስት አሳቤዎች አሉ። እነዚህም:-

1. ቴይዝም:- ዓለምን የፈጠረው እግዚአብሔር
2. ዴይዝም:- እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ትዱታል
3. ፓንቴይዝም:-
4. ፓንእንቴይዝም:- ይህን ዓለም የእግዚአብሔር አንደ ስጣል አድረጎ የሚያስብ ነው።
5. ኤትይዝም:- የእግዚአብሔርን መኖር የሚክድ አሳሌ

የፈጣሪን መኖር ለምን እናውቃለን?

1. ለመገለጥ (ለሕልም፣ ለራእይ፣ ቃሉን ለማሰማት፣ ለዘፈቀዱ ለመገለጥ)
2. ለተአምራትና ለሌሎችም ድንቆች የተገለጠውን እምኖ ለመቀበል
3. ለሥነ ፍጥረት
4. ለሥራው
5. ለመጽሐፍ ቅዱስ
6. ለተአምር
7. ለታሪክ
8. ለነገረ ሰጋው (በክርስቶስ ሰው መሆን)
9. ለጸሎት

ሃይማኖትና ሳይንስ

ሳይንስ ብቤተ ሙከራና ለተለያዩ ምርምሮች አማካኝነት የሚገኝ ዕውቀት ነው። ማለፊያን መሠረት ያደረገ ዕውቀት ነው። ሃይማኖት እግዚአብሔርን ለመመን ጥያቄታችን ተመራምሮ ለሰው ልጅ አገልግሎት ለማዋል የሚጸልገውን ሳይንሳዊ ምርምር አይቃወምም።
ሳይንስ እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ ተጠቅመን የሚገኝ ዕውቀት ነው። ስለዚህም ሳይንስ ሰላሉ ጥያቄታት ይናገራል እንጂ ከመጀመሪያው ጥያቄታችን እንዲኖሩ ያደረጋቸው ማን ነው ለሚለው ብቂ ምላሽ የለውም። የሳይንስ ቋሚ ዕውነት የለውም። ለሃይማኖት ግን ቋሚ እውነት አለው። በዓለም ላይ ሦስት ዓይነት አማኞች አሉ እነዚህም፦

1. ለትክክለኛ ሃይማኖት ያሉ (ኤፌ.4÷5)
2. በተሳሳተ እምነት ያሉ (ኤር.17÷5)
3. ምንም እምነት የሌላቸው (መዝ.13÷1)

የብዙ እምነቶች መፈጠር አንዱ ምክንያት የተጻፈውን ከዐውድ ለመለየት የራስን የተሳሳተ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ዕቅለተ እምነት

ዕቅለተ እምነት ማለት ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን እውነት ተቀብሎ መጠበቅና ለትውልድ ማስተላለፍ ማለት ነው። የዕቅለቱ እምነት ቁና ዓላማ ምእመናን ጉድለት ኖሮበት ሃይማኖት እውቀው ስለሌለው ትምህርት እንዲጠፋ ለማድረግ ነው።

የሃይማኖት ጥቅም

- ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት
- የተረጋጋ ሕይወትን ለመኖር
- ፈጣሪን ለማወቅ
- ረድኤትን ለማግኘት
- አየት እንዴመጣንና ለምን እንደምንኖር እንዲሁም መዳት እንደምንሄድ ለማወቅ

ሃይማኖት ለዘመናት

እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ ሃይማኖትም አንዲት ናት። የዚህች የአንዲ ሃይማኖት አማኞች ግን በየዘመናቱ የተለያዩ ስያሜዎች ነበሯቸው። በየዘመናቱ የተለያዩ ስያሜዎች የተሰጠው ያው አንዱ ሃይማኖት ነው እንጂ በየዘመናቱ የተመሠረቱ ሃይማኖት ኖሮ አይደለም። አማኝ፣ አይሁድ፣ ጸቅ መዛሙራት፣ ክርስቲያን፣ ኑሮታይክ፣ ተዋሕዶ።

የካቶሊክ ሃይማኖት ትምህርት ምንጮች

፩. መጽሐፍ ቅዱስ (Holy Bible)
፪. ቅዱስ ትውፊት (Holy Tradition)
፫. የቤተክርስቲያን አባቶች

ምንጭ ወይም መነሻ የሌለው ሐሳብ ጉሰቤተ ልብ (ልብ ወለድ) ይባላል።

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

አዕማድ ማለት ምሰሶዎች ማለት ነው። ምሥጢር ማለት ደግሞ ድብቅ፣ ሠውር፣ ረቂቅ ማለት ነው። አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

፩. ምሥጢረ ሥላሴ
፪. ምሥጢረ ሥጋዌ
፫. ምሥጢረ ጥምቀት
፬. ምሥጢረ ቁርባን
፭. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ምሥጢር የተባሉበት ምክንያት ለሚያምን ለእምነት የሚረዱ ለማያምን የተሠወሩ በመሆናቸው ነው።

ምሥጢረ ሥላሴ

ቅድስት ሥላሴ ማለት ብዙ ሦስትነት ማለት ነው። ይኸውም የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሦስትነታቸው ከፍጡራን የተለየ ሦስትነት ስለሆነ ነው።

አካላተ ሥላሴ

እግዚአብሔር ለአካለ ሦስት ሲሆን የእያንዳንዱ አካለ ዘለዓለም ደግሞ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው (ማቴ.28÷19)። ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ፍጹም አካል፣ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክ አላቸው። ሦስቱ አካላትም ለየራሳቸው ያንተው ይኖራሉ።

ባሕርየ ሥላሴ

ባሕርይ ማለት አካላዊ ህለዋ አካለ ማለት ነው። ይኸውም አካለ ያለሆነ፣ ለአካለ ግን ያለ ማለት ነው። የሦስቱ አካላት ለአንዳንት መገናዘብ ባሕርይ ይባላል (ሃይ.አበ.11÷9)።

ኩነታተ ሠላሴ

አብን ወይም ኩነት ማለት መሆን ማለት ነው። ኩነት ሊለዛ ኩነታት ይሆናል። የአብ የአብን ስም ብቻ ነው። የወልድ የአብን ስም ቃል ነው። የመንፈስ ቅዱስ የአብን ስም እስትንፋስ ነው። በኩነታት መገናዘብ አንደ መለያየት የለም።

አብ፦ ብቻ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ኃባቢ፣ አንባቢ ነው።
ወልድ፦ ቃል፣ ኃባቢ፣ አንባቢ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ሕያው፣ ማሕየዊ ነው።
መንፈስ ቅዱስ፦ ሕይወት፣ ሕያው፣ ማሕየዊ፣ ለባዊ፣ አለባዊ፣ ኃባቢ፣ አንባቢ ነው።

ግብረ ግሕርይ

ሦስቱ አካላት ማለትም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ተገናዝበው ለአንድነት የሚሠሩት ሥራ ግብረ ግሕርይ ይባላል (ሃይ. አበ. 53÷5)። ሦስቱ በግብረ ግሕርይ አንድ ናቸው። ይኸውም በምሰሶት፣ በዕውቀት፣ በማዳን፣ በርቀት፣ በዘለዓለማዊነት፣ በኃያልነት፣ በንጉሥነት፣ በግዕልነት፣ በዳድቅነት፣ በቅዱስነት፣ በታጋሽነት፣ በፈጣሪነት፣ በሁሉን ቻይነት፣ በክብር፣ በጥበብ፣ በፍቅር፣ በአምላክነት፣ በፀጉነት፣ በመጋረነት፣ በመሳሪነት፣ በፈታሒነት፣ በምስጋና፣ በአለመለወጥ እና በመሳሰሉ ካገሮች አንድ ናቸው ማለታችን ነው።

ግብረ ልደት (አካላዊ ግብር)

ሦስቱ አካላት ለአካላዊ ግብር ይለያያሉ። የአብ ግብሩ መውለድ፣ ማሠረጽ ነው። የአካላዊ ግብር ስሙ ወላዲ፣ አሠራጺ ነው። የወልድ ግብሩ መወለድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሠረጽ ነው።

ስመ አግዚአብሔር

የሦስቱ አካላት የአካል፣ የአካላዊ ግብር፣ የግብረ ግሕርይ፣ የአብን ስም እንዳሚከተለው ነው።

የአካል ስም	የአካል ግብር ስም	የአብን ስም	የግሕርይ ግብር ስም
አብ	ወላዲ፣ አሠራጺ	ልብ	አግዚአብሔር፣ ኤልሻዳይ፣ አጽናይ፣ ኤል፣ ኤሎሄ፣ ጸገም፣ አምላክ፣ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ንጉሠ...
ወልድ	ተወላዲ	ቃል	
መንፈስ ቅዱስ	ሠራጺ	እስትንፋስ	

መለኮት

በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮት የሚለው ቃል ብዙ ይተረጎማል። ለቃሩነት መለኮት ሦስቱ አካላት አንድ ለሚሆኑበት ግሕርይ ስም ይሆናል። መለኮት፦ መለክ=ገዛ ካለው ቃል ወጥቶ ፌትነት፣ ገዥነት ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።